refugee action

working with refugees to build new lives

**ምክር ተቀባዮች የሚያገኙት ጥቅም፣**

- ራስን ችሎ ለመኖር የሚያስፈልጉትን ጥበቦች ማዳበር
- ሊቨርፑልንና ሊቨርፑል ውስጥ ምን የት እንዳለ ማወቅ
- በራስ መተማመንን ማሳደግና ብቸኝነትን መቀነስ
- ስለብሪቲሽ ባሕል የላቀ እውቀትን ማዳበር
- ራስን ከሕብረተሰቡ ጋር ለማግባባት ምቹ ጊዜ ይፈጥርና ከአንዳንድ የችግር ሃሳቦች የሚመልስ ይሆናል
- ግብራዊ የሆኑ ምክሮችን መቀበልና የማሕበራዊ አገልግሎቶችን በቀላሉ ለማግኘት ይረዳል
- የእንግሊዝኛ ቋንቋን ለማሻሻልና በአነጋገር ላይ በራስ የመተማመንን ብቃት ያዳብራል

**ከላይ በዝርዝር ስላሉት ተመካሪው ስለሚያገኟቸው ጥቅሞች በይበልጥ ለመረዳት ከዚህ በፊት በነበሩ የምክር ሰጪ ፕሮጀክቶች ላይ የተሳተፉ የአንዳንድ ወጣቶች ንግግርን በማነፃፀሪያነት ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል።**

"መጀመርያ ወደሊቨርፑል ስመጣ ለኔ በጣም ከባድ ነበር ምክንያቱም ስለ ከተማይቱም ሆነ ስለ ሌላሰው የማውቀው ምንም አልነበረም። ነገርግን የምክር ሰጪ ፕሮጀችቱ ስለሊቨርፑል እንዳውቅና ከሰዎች ጋር እንድገናኝ ብዙ ረድቶኛል።"

"ስለ ብዙነገሮች ያግዛሉ እንደ የጂ.ፒ. ምዝገባ፣ የባንክ ደብተር መክፈትንና ተመዝግበህ ማጥናት የምትፈልገውን ኮርስ እንድታገኝ ይረዱሃል። እንዲሁም አዝናኝ የሆኑ ነገሮችን እንደ ወደ ሲኒማ ቤቶች መሄድን፣ ሙዚየሞችና የጉብኝት ጉዞዎችን ይሰጣሉ።"

“የምክር ሰጪ ፕሮጀክቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለመናገር እንድችል በራሴ ላይ መተማመንን አሳድሮብኛል።”

“የምክር ሰጪ ፕሮጀክቱ አዳዲስ ጓደኞችን እንዳገኝ ረድቶኛል።”

“በጣም አይነአፋርና የሚርበደበድ ነበርኩ፤ አሁን ግን በይበልጥ በራሴ ላይ የምተማመንና ደስተኛ ሆኛለሁ።”

“ከዚህ በፊት በጣም ብቸኛና ደስተኛ አልነበርኩም፤ ነገርግን ፕሮጀክቱ ከሰዎች ጋር እንድገናኝ ረድቶኝ የምሰራው ስራ ሰጥቶኛል። በጣም ደስተኛ እንድሆን አግዞኛል።”

“በእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታህ ላይና ባሕሉን ለማወቅ ያግዝሃል።”
“ሱቆች የት እንዳሉ እንዳውቅና ገንዝቤን እንዴት በስረአቱ ማስተዳደር እንዳለብኝ እንዳውቅ ረድቶኛል።”

**የምክር ሰጪዎች ጥቅም፣**

- የባሕል እውቀት አድማሱን ማስፋትና ስደተኛው በተደጋጋሚ የሚያጋጥመው አወያይ የሆኑ የጥያቄዎች እውቀትን ለማስፋት
- የመግባባት ዘዴዎችን ያዳብራል
- ፕሮጀችት አመራር ችሎታዎችን ያዳብራል
- ግላዊ ጥበቦችን ያዳብራል
- ከላይ የተጠቀሱትን ልምዶች በሙሉ ማሳደግ ለቅጥር ዝግጁነት ይረዳል

## የአንድ ምክር ሰጪ ትረካ

ፐ! ምክር ሰጪዎች። ዝግጁ ነበርኩ ወይ? ወደ ያቻ ምክር ሰጪ ፕሮጀክት ስገባ መጀመርያ የነበረኝ ሃሳብ ግልጽ ያልሆነና ብቻ ፍላጎቴ በሊቨርፑል ወጣት ስደተኞችንና ጥገኝነት ፈላጊዎችን የእንኳን ደህና መጣችሁ ስሜት እንዲያድርባቸው ማገዝ ነበር። ሃላፊነቱና ክርሱጋር አብሮ ለሚመጣው ስጋት ተጠያቂነቱን ግምት ውስጥ አላስገባሁትም ነበር፣ ነገርግን እንደገና ልወጣው እችላለሁ ወይ? በእርግጥ!

በመጀመርያ ያስጨነቀኝ አንድን ሰው በእውነቱ ለመርዳት ምን ማድረግ እንደምችል ነበር፣ ነገርግን ወዲያውኑ ልረዳው የቻልኩት አንድ ምክር ተቀባይ የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ፍላጎቱንና ምኞቱን አረጋግጠ እስኪያውቅ ድረስ አብሮት የሚዘልቅ፣ የሚረዳውና የሚያበረታታው ሰው ብቻ ነው። ይሔ አንዳንድ ጊዜ ብዙ የእግር ስራና ተስፋ ያለመቁረጥን ሊጠይቅ ይችላል፣ ነገርግን ስራው ላይ የተካተተው ነገር ቢኖር በቀላሉ ለመናገር ልክ እንደ ወደሚቀጥለው የጓደኛየ ቀጠሮ እንደምሄድ አይነት በበለጠ መዘጋጀትን ነው።

ከምክር ተቀባየ ጋር የነበረኝ ጓደኝነት አስደሳች ነበር። ምንጊዜም ቢሆን እንቀራረብ ነበር ለማለት አይደለም። በፕሮጀችቱ ላይ በተካተተው የገደባትና ድጋፍ አሰጣጥ ስርአትን በተመለከተ ስልጠናችን መሀል ላይ፣ የመጀመርያውን ጓደኝነቴን በጀመርኩበት ጊዜ ስሜታዊ ነክ በነበረው የምክር አሰጣጥ ጉዳይ ላይ በሚገባ ተዘጋጅቸ እንደነበር ይሰማኛል፤ ነገርግን ጓደኝነታችን እያደገ በሄደ ጊዜ የምክር ተቀባየን ያለፈ ታሪክ እንድታካፍለኝ የማበረታታት ምንም አይነት ፍላጎት ወይም ምኞት ፈጽሞ እንዳልነበረኝ ተገንዝቤአለሁ። እንደገና ሌላ እያደርኩ የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር እሷ ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ የምትወደው ያለፈ ታሪኳን ወይም ለምን ወደዚህ አገር እንደመጣች ምንም ከማያውቅ ሰው ጋር ነው። የምናወራው ስለ እሷና ስለ ልጇ መጻኢ እድልና ብቻ ነበር።

ምንድነው ጠቃሚ እንዲሆን ያደረገው?... በመጀመርያው የእናትና ህጻን ወገኖች ቀናቸው ላይ ህጻኑ ያንሁሉ አሻንጉሊት ሲያይ እፊቱ ላይ የነበረው አስተያየት... ከመጀመርያዋ የኮምፒዩተር ክፍል ስትወጣ በ’ኤም ፊትላይ የነበረው ደማቅ ፈገግታ። የመጀመርያው የምክር ሰጪነት ጓደኝነቴ እምብዛም ከባድ አልነበረም፣ ብዙውን ጊዜየን አልወሰደም፣ ሆኖምግን ምንጊዜም ከሰራኋቸው ስራዎች ይበልጡን ወሮታ ከፋይና ጠቃሚ ሊሆን የሚችል ነበር።

(Amharic)